## የ 2019–2020 መመሪያ

# መዋእለህፃናት በቅድሚያ ስለመግባት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

## አስቀድሞ መግባት

ቀደም ብለው ወደ መዋእለህፃናት እንዲገቡ ሪኮመንድ የሚደረጉ ልጆች ከእኩዮቻቸው ይልቅ ከሚጠበቀው በላይ ችሎታ ኖሯቸው አስቀድሞ ትምህርት መጀመርን ለማረጋገጥ እና በአካደሚክ፣ በማህበራዊ/ስሜታዊ እድገት እና በአካላዊ ዕድገት ማሳየት አለባቸው። ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ በመመደባቸው ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማረጋገጥ አስቀድሞ ለመግባት መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ከፍተኛ ናቸው። የተወለዱበት ቀን ከኦክቶበር 15 ባሻገር የሆኑ ልጆች፣ የይግባኝ ሂደትን ጨምሮ፣ ምንም አስተያየት አይደረግም።

መዋእለ ህፃናት/Kindergarten—በሴፐቴምበር 2 እና ኦክቶበር 15 መካከል 5 አመት እድሜ የሚሞላቸው ልጆች ወደ መዋዕለህፃናት በቀዳሚነት ለመግባት ተቀባይነት የማግኘት ብቃት ሊኖራቸው ይችላል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) COMAR 13A.08.01.02 እና የሜሪላንድ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ/Montgomery County Board of Education Policy JEB ይመልከቱ ወደ ቅድመ መዋእለህፃናት፣  መዋእለህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል ቀድሞ መጀመር  እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤት  (MCPS) ደንብ/Regulation JEB-RB፣ ቅድመ መዋእለህፃናት፣ መዋእለህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል አስቀድሞ መጀመር።

## አስቀድሞ ሙአለህፃናት መግባት

### የሙአለህፃናት ፕሮግራም ምንና ምን ያጠቃልላል?

የ MCPS መዋእለህፃናት ከሪኩለም መሠረት ያደረገው በተማሪዎች የማንበብ፣ የመጻፍ፣ እና የሒሳብ ብቃትን ማዳበር ላይ ሲሆን ለሁሉም ተማሪዎች ጠንካራ/ፈታኝ የትምህርት ልምዶችን/ተሞክሮዎችን ይሰጣል። ጥብቅ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም የሚያካትተው:-

- በየእለቱ ማንበብ/መጻፍ/የቋንቋ ስነጥበብ ማዕዘን/ምድብ
- በየእለቱ የሂሳብ ምድብ /ማዕዘን
- በየወቅቱ ግስጋሴን የመከታተልና ቀጣይ የትምህርት ፕላን ዝግጅት የማድረግ ግምገማ፣
- የአነስተኛ- እና የበርካታ-ቡድን ትምህርት፣ እና
- ራስን ችሎ/ለብቻ ለመማር የሚያስችሉ ድርጊቶች/እድሎች

የትምህርቱ ፕሮግራም በተጨማሪ ሳይንስ እና የማህበራዊ ጥናቶችን ይዘት ያካትታል፣ እንዲሁም  ተማሪዎች በስነጥበብ ሥራ፣ በሙዚቃ፣ በኢንፎርሜሽን ትምህርት፣ እና በጤና እና የሰውነት እንቅስቃሴ ትምህርቶችን ይጨምራል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን የአካባቢዎን ትም/ቤት በመገናኘት የሙአለህፃናት የትምህርት ክፍል ለመጎብኘት ቀጠሮ ያድርጉ።

## አስቀድሞ ሙአለህፃናት መግባት የተሻለ አማራጭ ነው ወይ?

### እባክዎን የሚከተሉትን ያገናዝቡ: -

- የአስቀድሞ መግባት ሂደት አላማ በ MCPS በሚከናወኑ ግምገማዎች አለካክ መሰረት፣ ከአማካይ በላይ አፈፃፀምና እድገት የሚያሳዩ ወጣት ልጆች ወደ ሙአለህፃናት እንዲገቡ ለማስቻል ነው። የልጁ/የልጂቱ አካዴሚያዊ ክህሎቶች እና ማህበራዊ/ስሜታዊ እድገት ግምት ውስጥ ይገባሉ።
- እነዚህ በእድሜ አነስተኛ ልጆች በመማርያ ክፍል ውስጥ በአንድ አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሚበልጧቸው ጋር አብረው መስራት መቻል ይኖርባቸዋል።
- ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ በመመደባቸው ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማረጋገጥ አስቀድሞ ለመግባት መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ከፍተኛ ናቸው።
- ት/ቤት አስቀድሞ መግባት ወላጆች/አሳዳጊዎች ለልጃቸው የሚያደርጉት የረጅም ጊዜ ውሳኔ ነው። በኤሌሜንታሪ፣ መካከለኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ከዚያም ባሻገር በሚያልፍበት ወቅት በልጁ/በልጂቱ ማህበራዊና/ስሜታዊው  ሁኔታ ላይ ምን አይነት እምቅ ተፅእኖ እንደሚያስከትል መተንበይ አይቻልም።
- አስቀድሞ ሙአለህፃናት መግባት የልጆች እንክብካቤ መተኪያ ማለት አይደለም። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጅ እንክብካቤ መረጃ፣ "LOCATE" መገናኘት ያስፈልጋቸዋል: - በአካባቢያቸው የተፈቀደላቸው የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ለሚፈልጉ ለChild Care በ 877-261-0060 እንዲደውሉ ወይም http://www.marylandfamilynetwork.org/what-is-locate%3A-child-care/ ይጎብኙ።

## ለምንድነው አስቀድመው የሚገቡ አመልካቾች ከሌሎች ሙአለህፃናት ከሚገቡ ልጆች ተለይተው ግምገማ የሚደረግላቸው?

በሜሪላንድ ስቴት ደንብ (COMAR 13A.08.01.02) መሠረት፣ ሴፐቴምበር 1 ላይ ወይም ቀደም ብሎ 5 ዓመት እድሜ የሚሞላቸው ልጆች መዋእለሕጻናት እንዲገቡ የዕድሜ ብቃት ይኖራቸዋል። በስቴት መመርያ መሰረት፣ የልደት ቀኑ በሴፐቴምበር 2 እና በኦክቶበር 15 መካከል የሆነ ልጅ ለአስቀድሞ መግባት ሊታሰብ ይችላል። የልደት ቀናቸው ከኦክቶበር 15 በኋላ ለሆኑ ልጆች ምንም ታሳቢ/አስተያየት አይደረግላቸውም። የልጅ ትውልድ ቀን ኦክቶበር 15 መስኮት ባሻገር ከሆነ የይግባኝ ሂደት አይኖርም።

በእድሜ ብቃት የሌላቸው ልጆች አስቀድሞ ሙአለህፃናት ለመግባት ብቁ ለመሆን በአካዴሚ አፈጻጸም ከመካከለኛ በላይ መሆናቸውንና እንዲሁም የማህበራዊ/ስሜታዊ እድገት ማሳየት ይኖርባቸዋል። ለአስቀድሞ የልጅነት እድገት ግምገማ ልጆች ማጥናት ወይም ዝግጅት ማድረግ አያስፈልጋቸውም። ግምገማዎቹ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የእድገት መስኮች የያንዳንዱን ልጅ አፈፃጸም የሚለኩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላሉ: -

- አካላዊ ደህንነትና የእንቅስቃሴ/motor እድገት
- ግላዊና ማህበራዊ እድገት
- የንባብና የቋንቋ ስነ ጥበብ እድገት
- የሂሳብ ትምህርት አስተሳሰብ

## ከማጣሪያ ሂደት ምን ሊጠበቅ ይችላል?

እያንዳንዱ ልጅ አንድ ግዜ ብቻ ነው ለመገመገም የሚችለው። ግምገማው የሚከናወነው በተወሰነው የአካባቢ ትም/ቤት ነው። በቀነ ቀጠሮ፣ ልጃቸው ጤነኛ እንደሆነ/እንደሆነች እና በግምገማ ድርጊቶች መሳተፍ እንደሚችል/እንደምትችል ማረጋገጫ የደህንነት መግለጫ ፎርም ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ልጆች በምልመላ እና በእንቅስቃሴዎች ላይ ከመሣተፋቸው በፊት ወላጆች/ሞግዚቶች አስቀድሞ ትምህርት ስለመግባት ሂደት ለልጃቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። መሳተፍ ማለት ለመጪው የትምህርት ዓመት  ወደ መዋእለህጻናት በቀጥታ ያስገባዋ(ታ)ል ማለት እንዳልሆነ ልጃቸው እንዲያውቅ/እንድታውቅ መርዳት አለባቸው። መግለጫ በሚሰጥበት ጊዜ የት/ቤት የማስተማር ሥራ ባልደረቦች የልጁን/የልጅቷን ሁኔታ ጥናት ያደርጋሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች በግምገማው ክፍለ ጊዜ ላይገኙ ይችላሉ። ትም/ቤቱ መቆያ ቦታ ያዘጋጃል። ውጤቶቹ የፈተናው እለት አይሰጡም። የት/ቤቱ ቡድን የግምገማውን አሃዞችና መረጃ ድህረ እይታ ያደርጉበታል እናም ከግምገማው በኋላ በ15 ቀኖች ውስጥ የፅሁፍ ማስታወቂያ ከውሳኔአቸው ጋር ይሰጣሉ። ልጃቸው ለአስቀድሞ መግባት ተመርጦ ከሆነ ትም/ቤቱ ወላጆቹን ተገናኝቶ ከትምህርት አመት መጀመርያ በፊት አስፈላጊ ለሆነው ስብሰባ ቀጠሮ ይይዛል።

## አንድ ወላጅ/አሳዳጊ ለሙአለህፃናት አስቀድሞ መመደብ እንዴት ማመልከት ይችላል?

- ልጃቸው ወደየትኛው የአካባቢ MCPS ት/ቤት እንደሚገባ/እንደምትገባ መጀመሪያ ወላጆች/ሞግዚቶች  ማወቅ/መወሰን አለባቸው። እርስዎ የሚኖሩበትን አካባቢ የሚያገለግለውን ት/ቤት ለማወቅ የድንበር/ክልል መረጃ/ኢንፎርሜሽን መስመር በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4710፣ ከ 9:00 a.m. እስከ 12:00 p.m ከሰኞ - ዓርብ ይደውሉ። በተጨማሪ በ MCPS ድረ-ገጽ የሚገኘውን የት/ቤት ምደባ ትር፡- www.montgomeryschoolsmd.org፣ የት/ቤት ምደባ መፈልጊያ መረብ ለመጠቀም ይችላሉ። የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy JEA፣ Residency, Tuition, and Enrollment ይመልከቱ።
- ከዚያም ወላጆች/ሞግዚቶች ወደ መዋእለህፃናት ቀድሞ የመግባት ቅጽ/ማመልከቻ (MCPS Form 271-6, Application for Early Entrance to Kindergarten)መሙላት አለባቸው፣ እና በልጃቸው የአካባቢ ት/ቤት ስለ መዋእለህፃናት የመጀመሪያ-መግለጫ በሚሰጥበት ጊዜ ለመሣተፍ ቀጠሮ መያዝ አለባቸው።
- ማመልከቻውን ከሚከተሉት ቦታዎች ማግኘት ይቻላል፡-
  - አካባቢ ትምህርት ቤት
  - የMCPS ድረ-ገጽ በ http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/271-6.pdf
  - የኤሌሜንታሪ የተወሃደ ስርዓተትምህርት ቡድን ፅ/ቤት፣ ስልክ ቁጥር፡- 240-740-4090።
- ወላጆች/አሳዳጊዎች የተሞላውን ማመልከቻ በመተዋወቂያ ክፍለ ጊዜ ማምጣት አለባቸው።
- ማመልከቻዎች ከፌብሩዋሪ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ እንቀበላለን።

## ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ት/ቤቱ ውሳኔ ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

- ስለ ት/ቤቱ ውሳኔ ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የማጣርያ ውጤቶችን ሊወያዩባቸውና ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ ለመጋራት ከት/ቤቱ ርእሰመምህር ጋር ስብሰባ መጠየቅ ይችላሉ።

## ለአማራጭ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች የስቴቱ መመርያዎች ምንድን ናቸው?

- በ MSDE ደንቦች መሰረት፣ ሙአለህፃናት ለመግባት ልጆች ከሴፕቴምበር 1 በፊት 5 አመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው። በተጨማሪ ለህፃናት እንክብካቤ ት/ቤት ሴፕቴምበር 1 ሲደርስ  ልጆች 3 ወይም 4 አመት ወደ ት/ቤት /nursery school (3 አመት) ወይም ወደ ት/ቤት ፕሮግራም/nursery school program (4 አመት) የመሆን የእድሜ ብቃት ደንቡ ይጠይቃል።

## ተጨማሪ የሙአለህፃናት ፕሮግራም መረጃ የት ይገኛል?

ስለ መዋእለ ህፃናት ከሪኩለም ዝርዝር መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት እና ከፕሮግራሙ የሚጠበቀው ምን እንደሆነ ለማወቅ፣ወላጆች/ሞግዚቶች የ MCPS ድረ-ገጽ ላይ Kindergarten Information & Resources መጎብኘት ይችላሉ። www.montgomeryschoolsmd.org/info/enroll/Kindergarten.aspx

በሜሪላንድ ስቴት ከሪኩለም ከመዋእለህፃናት የሚጠበቁ ነገሮች፡- MSDE ድረ-ገጽ http://www.mdk12.org/instruction/commoncore/index.html ይጎብኙ።

በዘር፣ በጎሣ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ ብሔራዊ ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የስደተኝነት አቋም፣ ጾታ፣ የጾታ ማንነት፣ የጾታ መገለጫ፣ ፆታዊ አገላለጽ፣ የቤተሰብ/የወላጅ አቋም፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ የአካል/የአዕምሮ ስንክልና፣ ድህነት እና የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ/አቋም፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌሎች የህግ ከለላ የሚደረግላቸው ባህርዮችን መሠረት ያደረገ ማናቸውም ህገወጥ አድሎአዊነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤት (MCPS) የተከለከለ ነው። ስለ MCPS ፀረመድሎአዊነት አቋም ሙሉውን መግለጫ፣ ከመመሪያዎች እና ስለ አድሎአዊነት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ፣ ወይም አኮሞዴሽኖችን ለመጠየቅ የግንኙነት መረጃ በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል። http://www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination/።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

ሕትመት፡- Department of Materials Management for the Elementary Integrated Curriculum Team
ትርጉም፡- Language Assistance Services Unit • Department of Communications

0854.19 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 2/19 • 257

Copyright © 2019 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland